## ክላሚዲያ [KLAMYDIA]
ክላሚዲያ በግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፍ በሽታ ሲሆን በሽታው በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሳቢያ በፍትወተ-ሥጋ ብልቶች መካከል ወይም በፍትወተ-ሥጋ ብልትና በአፍ ወይም በፍንጥጣ ውስጥ ባለ ስስ ሽፋን መካከል ንክክ ሲኖር ነው። ለበሽታው መያዝ ምክንያት የሚሆነው በብልቶች፣ በሽንት ቱቦና በፍንጥጣ ውስጥ የሚገኙ ስስ ሽፋኖች ውስጥ መኖር ሚስማማው ባክቴሪያ ነው። በሽታው በዓይን ውስጥ ባለው ስስ ሽፋንም ሕመም ሊያመጣ ይችላል።

ኮንደምን በአግባቡ መጠቀም በበሽታው ከመያዝ ይከላከላል። የግብረ-ሥጋ ግንኙነቱ እስክፈጸም ድረስ ኮንዶሙ መውጣት የለበትም።

## ምልክቶች [Symptomer]
ክላሚዲያ የያዛቸው ብዙዎቹ ሰዎች ሕመሙ አይሰማቸውም። ስለሆነም በበሽታው መያዛቸውን አያውቁም። ክላሚዲያ ያለምንም የበሽታው ምልክት ለረጅም ጊዜ ምናልባትም ለብዙ ዓመታት ሊቀጥል ይችላል። ስለሆነም አዲስ የታወቀ ክላሚዲያ ለትዳር/ለፍቅር ታማኝ እንደ አለመሆን ተደርጎ መተርጎም የለበትም።

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሽንት ሲሸኑ የሚጠዘጥዝ ሕመም ይኖራቸዋል። ይህም በቀላሉ ከፊኛ የማቃጠል ሕመም ጋር ሊመሳሰል ይችላል፣ ይህም በወጣት ሴቶች አካባቢ የተለመደ ሲሆን በወጣት ወንዶች አካባቢ እስከዚህም ነው። በጣም አልፎ አልፎ ክላሚዲያ የአጥንት መጋጠሚያዎች ሕመም ያመጣል።

ሴቶች በተጨማሪም የወር አበባ ለውጥ ሊኖራቸው ይችላል፣ ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ሳቢያ ወይም በወር አበባ ጊዜ መሐል አንስተኛ የደም ፍሳሽ ይኖራቸዋል። የክላሚዲያ ባክተሪያ ወደ የዕንቁላል ቱቦአቸው በመዛመት ለምክነት ወይም ኪሮንክ ለሆነ የማኅፀን ሕመም ሊያመራ ይችላል። ስለሆነም ሕክምና ማግኘት እንዲቻል በበሽታው መያዝን ቶሎ ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። ወደ የዕንቁላል ቱቦዎች የመዛመቱ ምልክቶችም የሆድ የታችኛው ክፍል ሕመምና የሰውነት ትኩሳት መጨመር ይሆናል። እንዲህ ዓይነት ምልክቶች ሲታዩም በፍጥነት መታከም ያስፈልጋል።
አንዲት ሴት በወሊድ ጊዜ ክላሚዲያ ካለባት የተወለደው ልጅ በበሽታው ሊያዝና የዓይን ወይም የሳምባ ሕመም ሊይዘው ይችላል።

በሽታው የያዛቸው ወንዶች በሽንት ቱቦአቸው ውስጥ የሚጠዘጥዝ ሕመምና ፍሳሽ ይኖራቸዋል፣ በብልታቸው ጫፍ ላይ ሽፌታ ይወጣል፣ በብልታቸው ቱቦ ውስጥም አንስተኛ ሕመም ይሰማቸዋል፡ ፡ የክላሚዲያው ባክተሪያ ወደ የዘር-ፍሬ (ቆለጥ) ከተዛመተ የዘር-ፍሬአቸውን ከረጢት ሊያጠቃ ይ ችላል፣ ይህም በኃይል ያማል፣ ቀይ ይሆናል፣ እንዲሁም ያብጣል።

## ምርመራው [Undersøkelse]
የክላሚዲያ ምርመራ ናሙናዎች በጥጥ በተሸፈነ ጫፍ ከሽንት ቱቦና ከማሕፀን አፍ ይወሰዳል። ክላመዲያ በሽንት ምርመራም ሊታወቅ ይችላል። ይህም በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቦታች በሥራ ላይ እየዋለ ያለ የምርመራ ዘዴ ነው። ማንም ክላመዲያ ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚገመት ሕመም ያለው ቢመረመር መልካም ነው። በተጨማሪም ሁሉም ወጣት ሴቶችና ወንዶች ቀደም ካለው የክላሚዲያ ምርመራ ወዲህ ሌላ አዲስ የፍቅር ጓደኛ ሲያገኙ ቢመረመሩ መልካም ነው።

## ህክምናው [Behandling]
ክላሚዲያ በአንቲባዮቲክ ይታከማል። አንድ ሰው በሕክምና ላይ እያለና ድኖአል ተብሎ አንድ ሳምንት እስክሞላው ድረስ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማድረግ የለበትም።

ሕክምናው ካለቀ ከተወሰኑ ሳምንቶች በኋላም የክትትል ምርመራ ቢደረግ መልካም ነው።

**ነፃ ምርመራና ሕክምና** [Gratis undersøkelse og behandling]

**በተላላፊ በሽታዎች መከላከያ ሕግ መሠረት ክላሚዲያ ለሕብረተሰቡ ሁሉ አደገኛ ተላላፊ በሽታ ተደርጎ ይተረጎማል። ይህም ማለት ማንም ለነፃ ምርመራና ሕክምና መብት አለው። አንድ ሰው በበሽታው ከተያዘ አሁን ላለው (ላላት) ወይም ቀደሞ ለነበረው (ለነበራት) የፍቅር ጓደኛ ማሳወቅ በጣም አስፈላጊ ነው። በግብረ-ሥጋ ግንኙነት አማካይነት በሽታው ወደ ሌላ ሰው መተላለፉን ለማረጋገጥና ለማከም እንዲቻል ሐኪሙና በሽተኛው በመተባበር በሽታው የተዛመተባችውን መስመሮች ይከታተላሉ።**